# ከእንግዲህ እነዚያኑ ተቃዋሚዎች ነን የሚሉ አምነን እንታገል ውይንስ

# አዲስ ጠንካራና ፅኑ ፓርቲ እንፍጠር

አስተዋይ በቀለ

ለኢትዮጵያ የሚቀረቀው ኃይል በየቦታውና በየሁኔታው በገሃድም፣ በምስጥርም እየተወያየበትና እየተመካከረበት ያለው ጉዳይ በአርስቱ ላይ የተመለከተው የኢትዮጵያ ወቅታዊ የፓለቲካ ጥያቄ ነው።

በፓለቲካ ስትራቴጅ አንጻር የፓለቲካ ወሮበላነትና ቅሌት ከዋጠው፣መላቅጡን ከአጣው፣ ፍሬ አልባ ተቃውሞና ድርጅታዊ ድክመት መላቀቅ አለመቻል ትልቅ ታሪካዊ ስህተት ነው።ይህን የማይገነዘቡ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ደጋፊዎቻቸው ሁሉ አገሪቱንና ሕዝቡን እየጐዱ መሆኑን ማወቅ አለብን።

- የትኛው ድርጅት ነው ከወያኔ ጋር አቻ የሆነ የፓለቲካ ፓርቲ፣ አባለት፣ አሰራርና ባህሪ ያለው?
- የትኛው ድርጅት ነው ከመነሻው ጀምሮ እድገት እያሳየ፣ ሕዝብን በብዛት እያቀፈ፣ አገሪቱን እያዳረሰ፣እያደራጀ፣የመራ፣በሂስና ግለሂስ ራሱን እያጠራና እያጠናከረ የመጣው?
- የትኛው ድርጅት ነው ከገንዘብ አንጻር እንካን አስተማማኝ ምንጭ አደራጅቶ አዋጡልኝ ከማለት ከልመና ራሱን ያዳነ?
- እስቲንገሩን ከወቅቱ ሁኔታ አንጻር የትኛው ተቃዋሚ ድርጅት ነው የወጣት ኃይል እንቲፋዳ ማቀጣጠልና ሰላማዊ ሕዝባዊ አመጽ ማነሳሳትና ማጋየት የሚችለው ?
- የትኛው ድርጅት ነው በኢትዮጵያ ፣ በሕዝቦቿ፣በአገር ሉዓላዊነትና በብሔራዊ ጥቅሞቿ ላይ ከወያኔ የተለየ ጥርት ያለ የፖለቲካ አቋምና መስመር ያለው?
- የትኛው ድርጅት ነው መስዋዕትና በመሰዋዕትም ላይ መስዋዕትነትን ደርቦ ለመክፈል ቆራጥነትን የትግል ፅናት ያላቸው አባላትን በብዛትና በጥራት በአገር ውስጥና በውጭ ያደራጀና ያንቀሳቀሰ?
- የትኛው ድርጅት ነው ራሱን፣ አባላቱንና ደጋፊዎቹን ከወያኔና ከሌሎችም ኃይሎች፣ ሴራና ጥቃት ለመከላከል የሚያስችል ሰፊ የኢንተለጀንስ ፕሮፓጋንዳ መዋቅር፣ አደረጃጀትና እንቅስቃሴ ያለው?
- የትኛው ድርጅት ነው ለኢትዮጵያ በጐ አስተያየት ባላቸው መንግሥታት ዘንድ ተቀባይነት፣ ሁለ_ ገብ ድጋፍና እርዳታ ያገኘ ?
- የትኛው ድርጅት ነው በአገር ውስጥና በውጭ ያሉትን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለሰመረ ኅብረት፣ ለትግል አንድነትና ለመዕከላዊ አመራር በማብቃት ተቀባይነት፣ ተሰሚነትና ተከታይነት ያለው?

- የትኛው ድርጅት ነው በየረድፉ፣ በየሙያው ያሉ የኢትዮጵያን ምርጥ ልጆች ሰፊ እውቀት፣ያጋርና የመንግሥት ሥርዓት ልምድ ያላቸውን የፖለቲካ ተመክሮ ባለሙያዎች አሰባስቦ የያዘ፣ ያቀፈና የሚያሰራ ?
- የትኛው ድርጅት ነው ለምሳሌ፣" ልዋጭ_ ልዋጭ" እያለ መሃል ሕዝብ ውስጥ ገብቶ አገሪቷንና ሕዝቡን የሚቃኝና በወያኔ አስተዳደር ተቋማት ውስጥ የራሱን ሰዎች በምስጢር አስርጐ የሚያሰራና ለነገው ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ የኢትዮጵያ መንግሥት ቁጥጥር አስቦና አበክሮ የሚዘጋጅ ?
- ወ .ዘ. ተ. . .

  ከእስከ ዛሬዎቹ የፖለቲካ ተቃዋሚዎች ጋር ከእንግዲህ አብሮ መጓዝ ውድቀት፣ ውርደትና ሞት ነው። እስካሁን የትም አላደረሱንም። ዛሬም _ ነገም የትም አያደርሱንም። ሽንፈት በሽንፈት ላይ መከናነም ካልሆነ በስተቀር።

በማንኛውም እረድፍ ብቃትና ቆራጥነት ከሌላቸው ድርጅቶች ጋር ከመጓዝ ይልቅ ለምን በድርጅታዊ አውቃቀሩና ፅናቱ፣ በአባላቱ ስብጥርነት፣ በሕዝባዊነቱ፣በአገር ሉዓላዊነት አመለካከቱ፣በአገር ወዳድነቱ፣ በአመራር ስልቱ፣በማይታጠፍ ትግሉ፣ በቆራጥ መሰዋዕትነት ከፋይነቱ፣ብቃት፣ ጥራቱና ክሬደንሻል ያለው ሃቀኛ አዲስ ግዙፍ አስተማማኝ ፓርቲ አናደራጅም ? የሚለው የሕዝብ ጥያቄ እየጐላና ተቀባይነት እያገኘ ነው ።

ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ነፃ እናውጣ፣ እናድን ካልንና ከልብ በኃላፊነት ከቆረጥን ወደር የማይገኝለት እንደ ንሥር አሞራ በአሸናፊነት ነጥቆ የሚወጣ አውራና ሁነኛ ፓርቲ በፍጥነት በአገር ውስጥና በውጭ አገር መፍጠርና መደራጀት አለበት።

## ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !
## ምንጊዜም ኢትዮጵያ !